# ሐሰታዊ የመንፈስ ተሃድሶ

ዛክ ፑነን

እየሱስና ሐዋርያቱ ደጋግመዉ እንዳስጠነቀቁን የመጨረሻው ዘመን የሚከሰተው በተስፋፋ አታላይ ድርጊቶችና በብዙ ሐሰተኞች ነብያቶች ነው (ማቴ 24፡3-5፣ 11፡24፣1 ጢሞ 4፡1) ። እኛም ባለፉት አመታት ብዙዎቹን አይተናቸዋል።

ታድያ ለምንድን ነው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስትያኖች በነዚህ ሐሰተኛ ነብያቶችና በአስመሳይ የመንፈስ ቀስቃሾች የሚታለሉት? ለምንስ ነው ብዙ የሃይማኖት መሪዎች በስነ ምግባር ጉድለትና ስግብግብነት ላይ የሚወድቁት?

እኔ ከተገነዘብኳቸው ምልክቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው

1 በአሁኑ ዘመን በርካታ ክርስትያኖች አዲስ ኪዳን ምን እንደሚያስተምር በጥንቃቄ አላጠኑም። ስለዚህ የአዲስ ኪዳንን ትምህርት ሳይሆን የሃይማኖት መሪዎቻቸውን ትምህርት በጭፍን ይከተላሉ።
2 ከስነምግባር (መንፈሳዊ ህይወት) ይልቅ ተአምራትና መለኮታዊ ስጦታዎች የበለጠ ቦታ ይዘው ይገኛሉ።
3 ምድራዊ ሀብት ከመንፈሳዊ ሀብት የበለጠ ቦታና ክብር ተሰጥቶታል።
4 በእውነት ስሜት የሚነካ መንፈስ ቅዱሰን ከአእምሮ መታለልና ከራሳቸው ከሚፈልቅ ረብሻ መለየት አቅቷቸዋል። አሁንም እንደገና ምክንያቱ አዲስ ኪዳንን ጠንቅቆ አለመረዳት ነው።
5 አእምሮአቸውን የቀና አስተሳሰብ እንዲከተል በማሰልጠን (ከአእምሮአቸው የሚፈጥሩትን ጊዜያዊ ፈውስ) በእየሱስ ስም ከሚገኘው መለኮታዊ ፈውስ ጋር አምታተውታል ።
6 ከጌታ ከሚገኘው ውስጣዊ ደስታ ይልቅ በስሜት ተገፍቶ የሚገኝ ፍንደቃ እና ያልተለመደ (እንግዳ የሆነ) አካላዊ ክስተት ዋና ቁም ነገር ተሰጥቶታል።
7 የሃይማኖት መሪዎች ከእግዚአብሄር ጋር ካላቸው መንፈሳዊ ጉዞ የበለጠ ለሰው የሚሰጡትን የቤተክርስትያን አገልግሎት ዋና ቁም ነገረ ሰጥተውታል።
8 እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ከእግዚአብሄር ክብር ይልቅ ከሰው የሚያገኙትን ከበሬታ የበለጠ ቦታ ሲሰጡት እናያለን።

9 እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች የሚያተኩሩት ክርስቲያኖች ለክርስቶስ በፍፁም መገዛታቸው ላይ ሳይሆን ወደ ቤተክርስትያን በሚመጣው የህዝብ ብዛት ላይ ነው።

10 የሃይማኖት መሪዎች በቤተክርስትያን እራሳቸውን እንደ ሰራተኛ ቆጥረው ቤተክርስትያንን ከመገንባት ይልቅ የግል የሥልጣን አድማሳቸውን ማስፋትና የገንዘብ ግዛታቸውን (የንግድ ድርጅታቸውን) መገንባት በህይወታቸው የበለጠ ቦታ ይዞ ይገኛል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ድርጊቶች እየሱስ ካስተማራቸው ነገሮች በጣም የተቃረኑ ናቸው። አዲስ ኪዳንም ይኼንን “የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ” ብሎ ጠርቶታል። ክርስትያኖች ይህንን በጥራት (በጥሞና) ካልተመለከቱ እንደሚመጣ የሚጠበቀው ሐሳዊ መሲሕ በሐሰተኛ ድርጊቶችና በድንቅ ተአምራቶች በዚህ ዓለም መድረክ ሲመጣ በጭፍን ይቀበሉታል። በክርስቶስ መንፈስ መመራት ማለት ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች በተለየ መንፈስ መመራት ማለት ነው።

የሚከተለው አንቀጽ እየሱስ በማቴዎስ 7፡13-27 የጠቀሰውን ያስረዳል (ማቴዎስ ምዕራፍ 5-7 ያንቡ)። ‘አስቀድሜ እንደገለጽኩት ወደ ህይወት የሚወስደው መንገድ ደጁም የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነው። ይሁን እንጂ ደጁም ሰፊ መንገዱም ትልቅና ቀላል ነው ብለው ከሚነግሯችሁ ሐሰተኛ ነብያቶች ተጠንቀቁ።የባህሪያቸውን ፍሬ አስተውለን ከተመለከትን በቀላሉ ልንለያቸው እንችላለን። ለምሳሌ ከንዴት፣ሴትን አይቶ ከመመኘት፣ ገንዘብን ከመውደድና ምድራዊ ሀብትን በጣም ከመፈለግ ህይወታቸው ነጻ ነውን? እኔ እንዳደረኩት ስለነዚህ ነገሮች ያስተምራሉ? ( ማቴ5፡21-32፣ 6፡24-34)። እነዚህ ሐሰታዊ ነብያቶች ብዙ ተዓምራትና መንፈሳዊ ምልክቶችን ሊያደርጉ ይችሉ ይሆናል። ሰውንም በእርግጥ በስሜ ይፈውሱ ይሆናል። በመጨረሻው ቀን ግን የድብቅ ሃጥያታቸውን ስላልተዉ እኔንም እንደ ቅዱሱ ስላላወቁኝ ወደ ገሃነም እልካቸዋለሁ (ማቴ 7፡21-23) ።

የማይነቃነቅና የማይፈረስ በዓለት ላይ የተሰራ ቤተክርስትያን ለመገንባት ከፈለጋችሁ ግን ስለነዚህ ነገሮች ተጠንቀቁ (ማቴ 5-7)። ሕዝቦቻችሁ ትዕዛዛቶቼን ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ የስሜንም ስልጣን እንዲደግፋችሁ እሰጣችኋለሁ (ማቴ 28፡20፣18) ። ነገር ግን ይህንን ሰምታችሁ ካልታዘዛችሁ የሰራችሁት ቤተክርስትያን ምንም እንኳን ለሰው ትልቅና አስገራሚ ቢመስልም አንድ ቀን በእርግጥ ተንከታክቶ ይወድቃል (ማቴ 7፡25)።

ስለዚህ በዚህ የመጨረሻ ዘመን የማይነቃነቅና የማይፈረስ ቤተክርስትያን እንዴት መገንባት እንችላለን?

1. እየሱስ በተራራ ላይ ያስተማረውን ትክክለኛ ትምህርት ደጋግመን መስበክና መኖር አለብን።(ማቴ 5-7)

2. በኦሪት ህግ ሳይሆን በአዲስ ኪዳን መሠረት መኖር አለብን ።ስለዚህም የሁለቱን ቃል ኪዳናት ልዩነት በጥራት (በዝርዝር) ማወቅ ከዚያም አዲስ ኪዳንን መስበክ አለብን (2 ቆሮ 3፡6)።

በአሁኑ ጊዜ የሃይማኖት መሪዎች ከባድ ሃጢያት ላይ ሲወድቁ ራሳቸውን ለማሳመንና ለማጽናናት የተሳሳቱና በሃጥያታቸው የወደቁ የብሉይ ኪዳን ጻድቃንን እንደ ምሳሌ ይጠቀማሉ። ዳዊት ያመነዘረውንና ኤልያስ በጠና ያዘነውን እንደ ምሳሌ በመጠቀም 'እግዚአብሔር እነዚህን እንኳን መልዕክቱን ለማስተላለፍ ተጠቅሞባቸዋል' እያሉ ለጥቂት ጊዜ ከሰው ፊት ከተደበቁ በኋላ አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ። የጳውሎስን አሸናፊነትና እስከ እድሜው መጨረሻም በንጽህና መኖሩን ግን እንደ ምሳሌ አይጠቀሙም።

እነዚህ የሃይማኖት መሪዎችና እነሱንም የሚከተሉ ክርስትያኖች ያልገባቸው ነገር ቢኖር የኛ ምስሌዎች የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን እንዳልሆኑ ነው። በዚህ የፀጋ ዘመን ብዙ ተሰጥቶናል። ብዙ ከተሰጠውም ሁሉ እንዲሁ ብዙ ይጠበቅበታል (ሉቃስ 12፡48)። እንግዲህ ምሳሌያችን፣ የእምነታችንም ጀማሪና ፍጹም አድራጊ፣አስታራቂያችንም ዳዊትና ኤልያስ ሳይሆኑ እየሱስ ብቻ ነው።እየሱስ ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ምን ያህል እንደሚበልጥ በዕብራይስጥ 12፡1-4 በግልጽ ተጽፏል። ይሁን እንጂ በዚህ እውነት የሚኖሩና "እግዚአብሔር የሚበልጥ ነገር እንዳዘጋጀልን" የሚታያቸው በጣም ጥቂቶች ናቸው (ዕብራይስጥ 11፡40) ።

ሰይጣን ብልህና ጮሌ ጠላታችን ስለሆነ ማናችንም ካልተጠነቀቅንና ዝግጁ ካልሆንን እንደ ማናቸውም የሃይማኖት መሪዎች ልንሳሳትና በሃጥያት ልንወድቅ እንችላለን ። ስለዚህ የእኛ ደህንነት የሚገኘው አዲስ ኪዳን የሚያስተምረንን ሙሉ በሙሉ በመከተልና እራሳችንን ለእውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች በማቅረብ ነው።ለመንፈሳዊ መሪዎች እራሳችንን በፍጹም ማቅረብ አለብን ስንል እነዚህ መሪዎች ከላይ የጠቀስኳቸውን የተሳሳቱ ነጥቦች አንዱንም የማያደርጉ መሆን አለባቸው ማለቴ ነው። ሌሎች ሰዎች ከሚሰሯቸው ስህተቶች ከተማርን እኛም እነዚሁኑ ስህተቶች ከመድገም እንድናለን።

ስለዚህ እራሳችንን ሁል ጊዜ በጌታ ፊት ዝቅ እናድርግ። እንደ ዮሐንስ የተደበቀ ምስጢር (መለኮታዊ ራዕይ) የምናገኘው በዚህ ዓይነት ትህትና ነው (ራዕይ 1፡17) ። በትህትና ከኖርን ሃጥያትን ለመቋቋም የሚያስችለንን ፀጋ እንቀበላለን ( 1ጴጥ 5፡5)። መንፈስ ቅዱስም እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ሲገልፅልንና ሰለ እኛም እውነተኛ ሁኔታ ሲያሳወቀን ከሃጢያት እንድንድን እውነትን እንውደድ። በዚህም መንገድ እግዚአብሔር ከማንኛውም ዓይነት መታለል ይጠብቀናል (2 ተሰሎንቄ 2፡10-11)። አሜን።

***[Counterfeit Revival – (Amharic – Ethiopian)]***

**By Zac Poonen**